# ትርፍ አይገኝበት

ለውጥ መጣ ብለው ፣ ዛሬም የምናየው
ለዘመናት ባገር ፣ ስልጣን ላይ የቆየው
የደደቢት ቅፍቅፍ ፣ ወያኔ የቃኘው
ዘራፊና ገዳይ ፣ ዛሬም ጎጠኛ ነው
ከምናውቀው ውጪ ፣ አዲሱ ሰው ማነው
ከመለስ ሹመኞች ፣ የት ነው የተለየው
ተጨባጭ የሆነ ፣ ለውጡስ የት ነው ያለው ።

እንዲያው በግርግር ፣ በሩጫ ችኮላ
ወሬ በማጣፈጥ ፣ እንጀት የሚበላ
የህዝብ አጋር ሆኖ ፣ ለወገን ያደላ
ሚዛን የሚደፋ ፣ ችግር የሚከላ
ስራው ሳይሰራ ፣ በይሆናል መላ
ጠፋ እንዴት ይባላል ፣ እሾህ አሜኬላ
ህዝብ ላይ አንዣቦ ፣ የሞት አዋጅ ጥላ
ወያኔ አሰፍስፎ ፣ ዛሬም ለግንጠላ ።

ህዝብን እያስራበ ፣ ሰርቆ የሚያገሳ
ሰው የተመሰለ ፣ ተፈጥሮው እንሰሳ
ባገር ላይ ያመጣ ፣ የማይሽር ጠባሳ
እንደናቱ አውድማ ፣ እንደናቱ ማሳ
ድንበር ያፈረሰን ፣ አጋሰስ እሬሳ
አርቆ እማያስብ ፣ የዕውቀት አንካሳ
የገማን ስርዓት ፣ የገማውን ዓሳ
ማፈናቀል ሳይቆም ፣ አዋጅ ሳይነሳ
ልምጣ የሚሉት ነገር ፣ ይቅር አይነሳ ።

እዚያው ከመዲና ፣ የሚነግሩን ካለ
በመንገድ ሳይደክሙ ፣ ብንሰማው ምናለ
ልናዳምጥ እንጂ ፣ መቼስ አንወያይ
የተለየ ነገር ፣ ተዓምር አይታይ
ለጥያቄና መልስ ፣ እድል ስለማይኖር
አዳማጭ ለማግኘት ፣ አያስፈልግ መዞር
ካራት ኪሎ ሆነው ፣ መልክቱን ቢያሰሙ
ይሰማዋል ሰዉ ፣ እርስዎም አይደክሙ
ይህን በጥሞና ፣ ያገናዝቡትና
ዘመኑን በሰላም ፣ እንሻገርና
ያሰቡት ይሳካል ፣ ከርሞ ይመጡና ።

በተቀመጡበት ፣ ሕግ ፍትህ ካጣ
ዘራፊና ገዳይ ፣ ባግባብ ሳይቀጣ
የቀድሞ ሹመኛ ፣ ከስልጣን ሳይወጣ
ችግር ሳይቀረፍ ፣ ያገራችን ጣጣ
ስራ መቼ ጠፋ ፣ ካገር የሚያስወጣ
መረጋጋት ያሻል ፣ ቸር ቀን እስኪመጣ
ትርፍ አይገኝበት ፣ ኳስ ሜዳ ቢመጣ ።

ታዛቢው

May 29, 2018